# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## <u>የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)</u>
## <u>ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ) ሦስተኛ መደበኛ ጉባዔ የአቋም መግለጫ፤</u>

### <u>I. አጠቃላይ፤</u>

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ) ሦስተኛ መደበኛ ጉባዔ ሰኔ ፳፩ እና ሰኔ ፳፪ ቀን ፪ ሺህ ዓ. ም. (June 28 – June 29, 2008) ለሁለት ቀናት በአሜሪካ አገር ሜሪላንድ ውስጥ ተካሂዷል።

ድኅረ-ግንቦት ዘጠና-ሰባት በአገራችን በተከሰተው የተወሳሰበ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ለመወያየትና ኅብረቱ ይዞታውን በጥሞና መርምሮ ወቅቱ የሚጠይቀውን መጣኝ አደረጃጀት በመያዝ ሕዝብን ማዕከል ያደረገ እንቅስቃሴ ማድረግ ስለሚችልበት ለመምከር መስከረም ፬ እና ፭ ቀን ፪ ሺህ ዓ/ም በሲልቨር ስፕሪንግ ሜሪላንድ አራተኛ አስቸኳይ የብሔራዊ ሸንጎ ጉባዔውን ማካሄዱ ይታወሳል። በዚያ አስቸኳይ የሸንጎ ጉባዔ ላይ አብዛኞቹ የኅብረቱ አባል ድርጅቶች ኢዴኃኅ አወቃቀሩን ከግል ድርጅታዊ ሥራ ይልቅ የጋራና አገራዊ ትግሉን ባስቀደመ መልኩ አሻሽሎ አመርቂ እንቅስቃሴ ማድረግ የሚያስችለውን አደረጃጀት እንዲይዝ ስምምነት ላይ ደርሰው ነበር። ሆኖም ከአባል ድርጅቶች አንዱ ማለትም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) በአንዳንድ የውስጥ ችግሮች ምክንያት በጉዳዩ ላይ ያኔውኑ ለመወሰን እንደማይችልና የሁለት ወር ጊዜ እንዲሰጠው በጠየቀው መሠረት ኅብረቱ ለተለወጠው የአገሪቱ ሁኔታ መጣኝ አደረጃጀትና አወቃቀር እንዲኖረው ለመምከርና ተጠናክሮ ለመውጣት የተጠራ ያ ጉባዔ ለድርጅቱ ጥያቄ ክብደት በመስጠት ጉዳዩ በእንጥልጥል እንዲቆይ ተደርጎ ነበር።
እነሆ ከስምንት ወራት በኋላ የተጠራውና ሰኔ ፳፩ እና ፳፪ ቀን ፪ ሺህ ዓ/ም የተሰየመው ይኸ የኢዴኃኅ ብሔራዊ ሸንጎ ሦስተኛ መደበኛ ጉባዔ ዋና የመወያያ ነጥቡ (አጀንዳው) አራተኛው አስቸኳይ ብሔራዊ ሸንጎ በይደር ለያዘው የአወቃቀር ዓቢይ ጉዳይ እልባት ሰጥቶ በአሁኑ ጊዜ አገራችንንና ሕዝባችንን ወደ አጉል አቅጣጫ እየወሰደ ያለውን እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ለማስወገድ በሚደረገው ትግል ኅብረታችን ያለበትን ታሪካዊ ኃላፊነት በተሻለ ቅልጥፍና ለመወጣት ይችል ዘንድ እራሱን ብቁና ዝግጁ ለማድረግ ነበር። ይኸ ከሁለት ድርጅቶች በስተቀር ሌሎች አባል ድርጅቶች ሁሉ ሙሉ ተካፋይ የሆኑበት የሸንጎ ጉባዔ ዓለም-አቀፋዊ፣ አካባቢያዊና አገራዊ ወቅታዊ ሁኔታዎችን እንዲሁም ኅብረታችን የሚገኝበትን ይዞታ በዝርዝር መርምሮ፣ በእንጥልጥል ለቆዩ የኅብረቱ የውስጥ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቶ፤ ከተናጠል ድርጅት ይልቅ የአገርንና የሕዝብን ብሶትና ጥቅም ባስቀደመ መልኩ መታገል እንዲችል <u>በጥምረት</u> እንዲዋቀር ወስኖ፤ ለዚሁ አዲስ አወቃቀር የቀረበውን ንድፍ አፅድቆ በመቀበልና የአጭር ጊዜ የሥራ እቅድ አውጥቶ ስብሰባውን አጠናቋል።

ምንም እንኳ ይኸ መደበኛ ሸንጎ በሙሉ ስምምነትና የወቅቱ ሊቀ-መንበር አቶ ፋሲካ በለጠ በፊርማቸው ባስተላለፉት ጥሪ አባል ድርጅቶች ከቅርብም ከሩቅም ጥሪውን አክብረው

ዋና ጽ/ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁጥር (P.O.Box) 73796
Washington DC 20056-3796, U.S.A

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

በጉባዔው ላይ ቢገኙም፤ ከኅብረቱ አባል ድርጅቶች መኻከል ሁለቱ ማለትም የኢትዮጵያ መድኅን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ እና የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ከዳር እስከዳር በተለመደው የኅብረቱ የቆየናዴሞክራሲያዊ የአሠራር ዘይቤ አንዳንዴም በሙሉ ስምምነት አንዳንዴ ደግሞ በሁኔታዎች አስገዳጅነት በግልጽ አብላጫ ድምፅ በኅብረቱ ሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ የተወሰዱትን ልዩ ልዩ ውሳኔዎች "ፀረ-ዴሞክራሲያዊና ሕገ-ወጥ" ብለው በመፈረጅ በሸንጎው ላይ አልተገኙም። የኅብረቱ ሦስተኛ መደበኛ ብሔራዊ የሸንጎ ጉባዔ በሁኔታው ቢያዝንም በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ስብሰባውን ያለ ሁለቱ ድርጅቶች ለመቀጠል ወስኖ ቀጥለው በተዘረዘሩት የጋራ ጉዳዮች ላይ አጠቃላይ ግንዛቤዎችን ጨብጦ ቀጣዩን ትግል በተመለከተ የሚከተሉትን ውሳኔዎች አስተላልፏል።

## II. ግንዛቤዎች፤

1. የግንቦት ሰባት ቅልበሳን ተከትሎ በአገራችን እየተተከለ ባለው የአንድ ፓርቲን የበላይነት እያነገሰ ያለ አምባ-ገነን የአገዛዝ ሥርዓትና እሱም በወለደው ሽብር ምክንያት ዛሬ በአገራችን በፖለቲካው መስክ ምንም ዓይነት የተጠያቂነት ደብዛ ጠፍቶ ጥቂት አምባ- ገነኖች በአሻቸውና እንዳሻቸው የአገራችንን አንጡራ መሬት ለባዕዳን አሳልፈው የሚሰጡበት፤ ዜጎች ነጋ ጠባ በዘፈቀደ የሚታፈሱበት፤ ደብዛቸው የሚጠፋበት፣ የሚንገላቱበት፣ ወገኖቻችን በተለይም የነገዋ ኢትዮጵያ ተረካቢ ወጣት በአገሩ ተስፋውን አሟጦ በአመቺውና ባገኘው መንገድ ሁሉ ወደ ባዕድ አገሮች እየነጎደ ለአሰቃቂ ስደት እየተዳረገ ያለበት፤ ቅድመ-ግንቦት ዘጠና ሰባት ተንገዳግደው መቆም የጀመሩና በማቆጥቆጥ ላይ የነበሩ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ሕዝባዊና የሙያ ተቋማት እንዲከስሙ የተደረገበት፣ ሕዝባችን ከዕለት ዕለት እየሰፋና እየከፋ ለሚሄድ አሳፋሪ ረሃብ፣ እርዛትና ታይቶ ለማይታወቅ የኑሮ ውድነትና የሕይዎት መመሰቃቀል እየተዳረገ የሚገኝበት፤ በአንፃሩ ለኢሕአዴግ መሪዎችና ዙሪያቸውን ለተኮለኮሉ ጥቂት ደጋፊዎቻቸው የተቀየሱ የኤኮኖሚና ማኅበራዊ ፖሊሲዎች ከዕለት ዕለት ቁጥራቸው እየተበራከተ ያለበት፣ በውጭ ፖሊሲም በኩል የኢሕአዴግ መሪዎች በባዕዳን ግፊት ለባዕዳን ጥቅም ሲባል የአገራችንን ዳር ድንበር ማስከበር ሳይችሉ በሶማሊያ ውስጥ ጣልቃ በመግባት የኢትዮጵያ ልጆች ላላስፈላጊ አሰቃቂ መስዋዕትነት ከመዳረጋቸው አልፎ ለእስልምና እምነት እድገት ከፍተኛ አስተዋጽዕያ ያደረገችው አገራችን በእስላሙ ዓለም እንደ ጠላት ተፈርጃ "ጂሃድ" እንዲታወጅባት የሚያደርግ ሁኔታን በመጋበዝ የአገሪቱን አንድነት ይበልጥ የሚያናጋና ከፍተኛ አለመረጋጋትን የሚፈጥር አደገኛ ሁኔታን እየዋጁላት መሆኑን በቁጭት በመገንዘብ፤

2. ለዚህ አስከፊና ውስብስብ ሁኔታ የሚመጥን አፀፋ መስጠት የሚጠበቅባቸው የአገራችን ዴሞክራቶች ካለንበት ቀውስ አንፃር ሲታዩ እዚህ ግቡ ሊባሉ በማይችሉ ጥቃቅን ልዩነቶች በመቦጫጨቅና በውስጥ አጉል አተካራ ተጠምደው ዛሬ እንደ ሕይዎት እስትንፋስ በጣም የሚያስፈልገን የአገር-ወዳዶችና የዴሞክራት ኃይሎች አንድነት የውሃ ሽታ የሆነበት አሳፋሪ ሁኔታ ላይ መገኘታችንን በቁጭት በማሰብ፤ ይኸም አሳሳቢ ጉዳይ በሁሉም ዘንድ ተገቢውን ትኩረት አግኝቶ አስቸኳይ የጋራ ምላሽ ካልተሰጠበት የኢትዮጵያ አንድነት፣ ሰላም፣ ዴሞክራሲና ብልጽግና የቢባል ሕዝባዊና አገራዊ አጀንዳ የረባ ሰብሳቢ ኃይል አጥቶ ከግንቦት ሰማንያ-ሦስቱ ስመ-ጥፉ የለንደን ስብሰባ በከፋ መልኩ የአገራችን ዕጣ-ፈንታ ከሕዝባችን ተሳትፎና ከሁላችንም ራእይ ውጭ ሊወሰን የሚችልበት እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ መሆናችንን በማጤን፤

ጉባዔው የሚከተሉትን ውሳኔዎች አስተላልፏል።

## III. ውሳኔዎች፤

1. ታሪካዊውን የግንቦት ዘጠና-ሰባት ተከትሎ የተከሰተው ሁኔታ ኅብረታችን ሲመሠረት ከነበረው በእጅጉ የተለየ በመሆኑና ይኸም ኅብረቱ ብሔራዊ ኃላፊነቱን እርባና ባለው መልክ ለመወጣት እንዲችል የተለወጠውን ሁኔታ የሚመጥን አወቃቀርንና አደረጃጀትን መያዝ የግድ ስለሚጠይቅ፣ ቀደም ሲል በአራተኛው የኅብረቱ ብሔራዊ ሸንጎ አስቸኳይ ጉባዔ በሰፊው የአሳብ ልውውጥ በተደረገበት መሥመር ይኸም ሦስተኛ መደበኛ ጉባዔ በዋና አጀንዳነት ጊዜ ወስዶ የተወያየው በዚሁ የመዋቅር ለውጥ ላይ ነበር። ይኸንኑ ዓቢይ ጉዳይ የኅብረቱ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 6 እና አንቀጽ 8 የተደነገጉትን መሠረት በማድረግ ጉባዔው ኅብረቱ እስካሁን ይዞት የቆየው አወቃቀር እንዲሻሻልና አባል ድርጅቶች በበጎ ፈቃዳቸው ከየግል ድርጅታዊ ዓላማና እንቅስቃሴ ይልቅ **ለጋራው አገራዊ ትግል ቅድሚያ መስጠትን** በሚጠይቅ አደረጃጀት ማለትም <u>በጥምረት</u> እንዲዋቀር ጉባዔው ወስኗል። ( በዚህ ጉዳይ ላይ ዝርዝር ሁኔታውን በተመለከተ በኅብረቱ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ቀጣይ ማብራሪያዎች ይሰጣሉ።)

2. ቀጣዩ የትግላችን መነሻ ነጥብ በግንቦት እንቅስቃሴ መልክ <u>ሕዝባችንን መልሶ የትግሉ ባለቤትና ማዕከል</u> የማድረግን ተልዕኮ የያዘ ነው። በዚህ መሠረት የሕዝባችንን የትግሉ ባለቤትነትና ማዕከልነት ጉዳይ ቁልፍነት በመገንዘብ ኢዴኃኅ <u>"ሰላማዊ ሕዝባዊ ትግል"</u> በሚለው መርኅ መሠረት የኃይሎች መሰባሰብንና የተሻለ አደረጃጀትን የሚጠይቅ አጠቃላይ የግብ ትልም (ስትራቴጂ) ነድፎ ለመንቀሳቀስ ወስኗል።

3. ኅብረታችን (ኢዴኃኅ) በዚህ ታሪካዊ ሸንጎ ሳቢያ ለአገራዊው ትግል አባል ድርጅቶች ከድርጅታዊ ነፃነታቸው ቀንሰው ለጋራ ተጋድሎ እራሳቸውን ያመቻቹበት ሁኔታ ቢፈጠርም፣ ማንም ይሁን ማንም ድርጅት ለዚህ "ሰላማዊና ሕዝባዊ ትግል" ከአስተዋጽዖ አልፎ በብቸኝነት የሚፈይደው ምንም የረባ ነገር እንደማይኖር አጥብቆ ያምናል። ከዚህ እምነት በመነሳት ትግላችን የዚች አገራችንና የዚህ ሰማዕት ሕዝባችን ጉዳይ ያገባናል የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክና የሙያ ስብስቦች፣ የሐይማኖት መሪዎች፣ ምሁራንና አገር-ወዳድ ዜጎች፣ ወዘተ… ሁሉ የጋራ ኃላፊነት በመሆኑ በመከባበርና በወንድማማችነት/ እህትማማችነት መንፈስ እነዚህ ኃይሎች በአስቸኳይ ተሰባስበውና መክረው <u>የጋራ ትግል መድረክ</u> መፍጠራቸው ከእንግዲህ በምንም ዓይነት በይደር ሊተላለፍ የማይችል የታክ ኃላፊነት ነው ብሎ ኢዴኃኅ ያምናል። በመሆኑም እነዚህን ኃይሎች ያካተተ አንድ ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ የሚጠራበትን ሁኔታና ዘዴ ለማመቻቸት ይቻል ዘንድ <u>የጋራ አዘጋጅ አካል</u> ማቋቋም የሚችል ለጊዜው ፈቃደኛ በሆኑ ወገኖች አማካይነት አንድ <u>ጊዜያዊ የምክክር አካል</u> እንዲቋቋም አስፈላጊ እንደሆነ እምነታችን ነው። በዚህ ረገድ ኢዴኃኅ ይኸንን ለረጅም ጊዜ በይደር ሲንከባለል የቆየንጉዳይ ሁኔታው በሚጠይቀው ፍጥነት እውን እንዲሆን የበኩሉን አስተዋጽዖና አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ወስኗል።

## IV. ልዩ ልዩ፤

1. ከኅብረቱ ምሥረታ ጀምሮ አባል ሆነው የቆዩት ሁለት ድርጅቶች (የኢትዮጵያ ሕዝብ ፌዴራል ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ-ኅብረሕዝብ እና የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት -ኢዴኅ) መዋኃዳቸውንና በኅብረቱ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ በአዲሱ ድርጅታቸው በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ

ብቻ እንደሆነ በጉባዔው መክፈቻ ላይ በመግለጻቸው ጉባዔው ጥያቄአቸውን በደስታ ተቀብሎ ተሳትፏቸው በአዲሱ ድርጅታቸው በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ የአንድነት ንቅናቄ ስም እንዲሆን አጽድቋል፡፡

2. የኅብረቱን ዴሞክራሲያዊ ውሳኔ በመርገጥ በጉባዔው ላይ ያልተገኙትን ሁለት ድርጅቶች (ኢሕአፓና መድኅን) በተመለከተ አቋማቸውን የአገርንና የሕዝብን ጥቅም ባስቀደመ ሁኔታ እንደገና መርምረው የብዙኃኑን ውሳኔዎች እያከበሩ የመሥራትን ዴሞክራሲያዊ ባህል ተላብሰው ወደ ጋራው የትግል መድረክ እንዲመለሱ ጥሪ እንዲደረግላቸው ጉባዔው ወስኗል፡፡

3. ኅብረተ ባፀደቀውና ከአሁን በኋላ በሚከተለው አዲሱ የጥምረት መዋቅር መሠረት የኅብረቱ ብሔራዊ ሸንጎ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲጠራ ወስኗል፡፡

4. አዲሱ የኅብረት ብሔራዊ ሸንጎ እስከሚጠራ ድረስ የኅብረቱ ተግባር ቀጣይነት እንዲረጋገጥ ጊዚያዊ አመራር እንዲሰየም በተወሰነው መሠረት የኅብረቱ ኃላፊዎች በጉባዔው ተመርጠዋል፡፡

በመሆኑም፡-

ሀ) አቶ ኦባንግ ኡኩሞ - የኅብረቱ ሊቀ-መንበር፣
ለ) አቶ ኃይለ-ገብርኤል አያሌው - ምክትል ሊቀ-መንበር
ሐ) አቶ ደረጀ ከበደ - ዋና ፀሐፊ
መ) አቶ ሙሉጌታ ኃይሉ - የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ

ሆነው እንዲሠሩ ተመርጠዋል፡፡

ከድርጅት አገር ይቅደም!
ኅብረት ለድል፣ ድል በኅብረት!!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ)

ሰኔ ፳፫ ቀን ፪ ሺህ ዓ/ም
ዋሽንግተን ዲ.ሲ. አሜሪካ